የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፫
አዲስ አበባ–ጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 3
ADDIS ABABA 24th October, 2002

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፩/፲፱፻፺፭ ዓ·ም
ለመዋቅር ማስተካከያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ........................ ገጽ ፩ሺ፱፻፴፩

## CONTENTS

Proclamation No. 291/2002
International Development Association Credit Agreement for Financing Structual Adjustment Program Ratification Proclamation ......... Page 1931

### አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፩/፲፱፻፺፭
### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለመዋቅር ማስተካከያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ·ዲ·አር· ፺፮ ሚሊዮን ፪፻ሺ (ዘጠና ስድስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ ኤስ·ዲ·አር) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ·ኤ·አ· ጁን ፳፯ ቀን ፪ሺ፪ በዋሽንግተን ዲ·ሲ· የተፈረመ በመሆኑ፤

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ውሎች ተፈፃሚ ከመሆናቸው በፊት መፅደቅ ስላለባቸው፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «ለመዋቅር ማስተካከያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፩/፲፱፻፺፭» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### *PROCLAMATION NO.291/2002*
### *A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION*

WHEREAS, a Credit Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit amount of SDR 96,200,000 (Ninety Six Million Two Hundred Thousand Special Drawing Rights) for financing Structural Adjustment Program, was signed in Washington D.C., on the 27th day of June, 2002;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Credit Agreement at its session held on the 24th day of October, 2002;

NOW, THEREFORE, in accordance with Sub-Articles (1) and (12) of Article 55 of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

   This Proclamation may be cited as the "International Development Association Credit Agreement for Financing Structural Adjustment Program Ratification Proclamation No. 291/2002."

ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ «የብድር ስምምነት» ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ጁን ፳፯ ቀን ፪ሺ፪ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የተፈረመው ቁጥር ፫ሺ፮፻፷፮ – ኢ.ት. የብድር ስምምነት ነው።

፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ኤስ.ዲ.አር. ፺፮ ሚሊዮን ፪፻ሺ (ዘጠና ስድስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል

፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Credit Agreement" means the Credit Agreement Number 3666-ET signed in Washington D.C., on the 27th day of June, 2002 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association.

3. *Power of the Minister of Finance and Economic Development*

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Credit amount of SDR 96,200,000 (Ninety Six Million Two Hundred Thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 24th day of October, 2002.

Done at Addis Ababa, this 24th day of October, 2002.

GIRMA WOLDE GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE